# የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 22/2000

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀጽ 22 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 22/2000» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. ት ር ጓ ሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

3.1 «ቀጥተኛ ላኪ» ማለት የወጪ ምርቶችን በማምረት ወይንም ካመረቱት በመቀበል ወደ ውጭ የሚልክ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

3.2 «ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ» ማለት ምርቱን በጥሬ ዕቃ ወይም ባለቀለት ዕቃ መልኩ ወይም ከውጭ ያመጣውን ጥሬ ዕቃ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ለቀጥተኛ ላኪ በግብአትነት የሚያቀርብ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

3.3. «አዋጅ» ማለት የተሻሻለው ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 543/99 ነው።

3.4 ሌሎች ቃላትና ሐረጉች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

## 4. ወደ ውጭ ስለመላክ

በአዋጁ አንቀጽ 2(3) መሠረት አንድ ዕቃ ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ተጫነ የሚባለው፣

1. መድረሻው ከኢትዮጵያ ውጭ በሆነ የአየር ማጓጓዣ ላይ መጫኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ ወይም

2. የጠረፍ ጣቢያዎችን አልፎ ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጀ ባቡር ወይም የየብስ ማጓጓዣዎች ላይ መጫኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ ወይም

3. በማንኛውም ወደብ መርከብ ላይ እንዲጫን የኢትዮጵያ የጉምሩክ ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ ሲያሳልፈውና መርከብ ላይ መጫኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው።

## 5. የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተፈጻሚነት

በአዋጅ ቁጥር 543/99 የተደነገጉት የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች:-

1. እንደአግባብነቱ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ወይም በቫውቸር ዋስትና ከገቡ በኋላ አስመጪው በሚረከብበት ጊዜ የተሳሳቱ፣ የጐደሉ ወይም የተበላሹ እንዲሁም በአገር ውስጥ ገዥ ያጡ መሆናቸው በመረጋገጡ ወደመጡበት ለሚመለሱ ጥሬ ዕቃዎችና ሸቀጦች ፣

2. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦችን በሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ለሚመረቱ ወጪ ምርቶች ለሚውሉ ከውጭ አገር የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎችና በከፊል የተፈበረኩ ዕቃዎች፣

3. ለውጭ ገበያ ለሚውሉ ሸቀጦች መያዣ ወይም መጠቅለያ ለሚያገለግሉ ዕቃዎች፣

4. በላኪነት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ወደ ውጭ ለሚልኳቸው በአገር ውስጥ የተመረቱ ሸቀጦች፣

5. ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተቋቋሙ ድርጅቶች በቀጥታ በማምረት ተግባር ላይ እንዲውሉ ወደአገር ለሚያስገቧቸው ዘይቶች፣ ቅባቶችና ሌሎች ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮች፣

6. ለውጭ ገበያ ለሚውሉ ሸቀጦች ማምረቻ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን ለማምረት እንዲውሉ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ ለሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## 6. <u>የቫውቸር ሥርዓት</u>፣

### ሀ. ቫውቸር

1. የቫውቸር ደብተር ወደሀገር በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች፣ ማሸጊያዎችና መጠቅለያዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ለማቀናነስ እና ቀረጡ በተቀነሰ ቁጥር የሚቀረውን ሂሣብ ለመመዝገብ የሚያገለግሉ ሠንጠረዦችን ይይዛል።

2. ከተፈቀደለት ባለመብት በስተቀር ለሌላ ወገን የማይተላለፍ ነው፣

3. በቫውቸር ደብተሮች ላይ የተጠቃሚው ስም፣ አድራሻ፣ የቫውቸር የምስክር ወረቀት ቁጥር እና የቫውቸር ደብተሩ መለያ ቁጥር ይሞላል፣

4. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ቫውቸሩን በጥንቃቄ የመያዝ እና ቫውቸሩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢጠፉ ይህንኑ ለጉምሩክ ባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፣

5. የቫውቸር ተጠቃሚዎች ቫውቸሩ የጠፋባቸው መሆኑን የሚገልፅ መረጃ ከፖሊስ ጣቢያ ካቀረቡ የጉምሩክ ባለሥልጣን ቫውቸሩ ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲያውቁ በማድረግ በምትኩ ሌላ ቫውቸር ይሰጣል።

## ለ. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3፣ 5 እና 6 ሥር የተዘረዘሩትን ዕቃዎች በቫውቸር ዋስትና ማስገባት የሚችሉት በአዋጁና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እና በወቅቱ አሳድሰው የተገኙ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ናቸው።

2. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የቫውቸር የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት ከአገር ውስጥ የሚገዙትን እና ከውጭ አገር የሚያስመጡትን ጥሬዕቃ ዓይነት፣ መጠንና ዋጋ ዝርዝር ማቅረብ አለባቸው።

3. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ወደውጭ ለሚላኩ ሸቀጦች ማምረቻ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎችን፣ መያዣዎችንና መጠቅለያዎችን ወደአገር ማስገባት የሚችሉት የተሰጣቸውን የቫውቸር ደብተር ለጉምሩክ

ባለሥልጣን አቅርበው በደብተሩ ላይ መጀመሪያ ከተመዘገበው ወይም በየጊዜው በቀሪነት ከሚታየው የቀረጥ ሂሣብ ላይ ወደ አገር ውስጥ በሚያስገቡት ዕቃ ላይ የሚከፈለውን የቀረጥ መጠን እንዲቀናነስ በማድረግ ነው፡፡

4. ምርታቸውን ወደ ውጪ የሚልኩ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የወጪ ምርቱን ለማምረት በአገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን የሚጠቀሙ ሲሆን፣ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የአገር ውስጥ ታክስ በመክፈል ምርቱ ወደውጭ ከተላከ በኋላ ማስረጃዎችን በማቅረብ የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡

## ሐ. የቫውቸር ሥርዓት ዝርዝር አፈጻጸም፣

1. በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጉምሩክ ባለሥልጣን የቫውቸር ደብተሮች ያሣትማል፡፡

2. የጉምሩክ ባለሥልጣን ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚቀርብለት ማስረጃና ከተጠቃሚው በሚቀርብለት የምስክር ወረቀት መሠረት ለሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የቫውቸር ደብተር ይሰጣል፡፡

3. የጉምሩክ ባለሥልጣን ለተጠቃሚዎቹ የሰጣቸውን የቫውቸር ደብተሮች መለያ ቁጥር፣ የተጠቃሚዎችን ስምና አድራሻ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ለተጠቃሚዎች የተሰጡትን የቫውቸር የምስክር ወረቀቶች ቁጥር እና የተጠቃሚዎችን የቀረጥ ሂሣብ መዝግቦ ይይዛል፣ ይህንኑም ለገቢዎች ሚ/ር እና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

4. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች አድራሻቸውን በሚለውጡበት ጊዜ አዲሱን አድራሻቸውን ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፣

5. የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደውጪ ለሚላኩ ሸቀጦች ማምረቻ ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች፣ መያዣዎችና መጠቅለያዎች ላይ ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ የተሰጣቸውን የቫውቸር ደብተር ለጉምሩክ ጣቢያዎች አቅርበው እንዲቀናነስ በማድረግ ዕቃዎቹን መረከብ ይችላሉ፡፡

## መ. ቫውቸር የተሰጠበትን የቀረጥ ሂሣብ ስለማወራረድ፣

1. በቫውቸር ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(ለ) መሠረት በቫውቸር ዋስትና ከውጪ አገር ባስገባቸው ዕቃዎች ያመረተውን ምርት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደውጭ መላኩን የሚያረጋግጡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 (ሠ) የተመለከቱትን ማስረጃዎች ዋናውንና ኮፒውን ለጉምሩክ ባለሥልጣን በማቅረብ የቫውቸሩን ሂሣብ የማወራረድ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. የቀረቡት ማስረጃዎች በጉምሩክ ባለሥልጣን ከተመረመሩና ሊወራረድ የሚገባው የቀረጥ ልክ በተናጠል የተመላሽ ቀረጥ ስሌት መሠረት ከተሰላ በኋላ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚው የቀረጥ ሂሣብ በጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲወራረድ ይደረጋል፣ የተወራረደውን የቀረጥ ሂሣብ መጠን በዝርዝር የሚያሳይ ሪፖርት በየሦስት ወሩ ለገቢዎች ሚኒስቴር እና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይላካል፡፡

3. የጉምሩክ ባለሥልጣን የማስረጃዎችን ኮፒ ከኦሪጅናሉ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ተሰልቶ ለቀረበው ወደውጭ አገር ለተላከው ምርት በዋለው ጥሬ ዕቃ፣ ማሸጊያና መጠቅለያ መጠን የተጠቃሚውን ሰው ወይም ድርጅት ቫውቸር ይወራረዳል፣ በቫውቸር ደብተሩም ላይ «የተወራረደ» የሚል ማህተም ይደረግበታል።

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6-ለ-2 መሠረት የቫውቸር ዋስትና ተሰጥቶበት ወደ አገር ውስጥ በገባ ጥሬ ዕቃ የተመረተው ምርት ወደአገር በገባ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ ካልተላከ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 11(7) ይህ የጊዜ ገደብ ተራዝሞ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ምርቱ ወደ ውጭ ለመላኩ ማስረጃዎች ለጉምሩክ ባለሥልጣን ቀርበው ቫውቸሩ እንዲወራረድ ካልተጠየቀ ዋስትናውን ያስያዘው ሰው ወይም ድርጅት ወደ አገር በገባው ዕቃ ላይ ሊከፈል ሲገባ የታለፈውን ቀረጥ ከነወለዱ ይከፍላል።

5. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቀሚ የሆነ ሰው ወይም ድርጅት ሥራውን በማቋረጡ ምክንያት የቫውቸር ደብተሩን የመለሰ እንደሆነ «ያልተሰራበት» የሚል ማህተም ተደርጎበት በጉምሩክ ባለሥልጣን በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡

## ሠ. ቫውቸርን ለማወራረድ የሚቀርቡ ማስረጃዎች፣

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በቫውቸር ዋስትና ከውጭ አገር ባስመጧቸው ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የቀረጥ ሂሣብ ለማወራረድ ጥያቄአቸውን ለጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ዋናውን እና ኮፒውን አሟልተው ማቅረብ አለባቸው።

1. ወደውጭ የተላከውን ምርት ለማምረት የሚያስፈልጉ ከውጭ የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎችና ሌሎች ግብዓቶች ዝርዝርና የተወሰነ መጠን ወጪ ምርት ለማምረት የተጠቀመባቸውን ግበዓቶች/የግብዓት ምርት ጥመርታ/ ለምሳሌ:- አንድ የቆዳ ጫማ፣ አንድ የቆዳ ጃኬት፣ አንድ መቶ ጠርሙስ የወይን ጠጅ፣ ወዘተ/

ለማምረት ከእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች (inputs) የሚያስፈልገውን መጠን የሚያረጋግጥ በአምራቹ የተዘጋጀና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማረጋገጫ የተሰጠበት መግለጫ፣ (ይህ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የግብዓት-ምርት ጥመርታ (Standard Input-Output coefficient) ሲዘጋጅ የሚቀር ይሆናል)

2. ከውጭ አገር ለገቡ ጥሬ ዕቃዎችና መያዣዎች/ መጠቅለያዎች፣ የዕቃውን መጠን፣ ዋጋ፣ የገባበትን ጊዜና የተከፈለውን የታክስ መጠን የሚገልፁ፣

- የጉምሩክ ዲክላራሲዮን፣
- ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣
- በቀረጡና በታክሱ ልክ የተቀናነሰውን ሂሣብ የያዘውን የቫውቸር ደብተር፣
- የዕቃ ዝርዝር (packing list)

3. ከውጭ አገር በገባውና አገር ውስጥ በተመረተው ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች የተመረተው/ የተዘጋጀው ምርት ለውጭ ገበያ መላኩን የሚያረጋግጡ፣

- የጉምሩክ ዲክላራሲዮን

- ደረሰኝ (Commercial Invoice)

- ምርቱ ከተላከ ከ3 ወር በላይ ከሆነ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ገንዘብ የተከፈለበት የባንክ ደረሰኝ (Bank Credit Advice)

4. ቫውቸርን ለማወራረድ የሚቀርቡ ሰነዶች እንዲሁም የተሠራባቸው እና ያልተሠራባቸው ቫውቸሮች አጠባበቅና አወጋገድ ስለፋይናንስ መዛግብት አጠባበቅ የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 5/91 መሠረት በማድረግ ይከናወናል፡፡

## 7. <u>ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚደረግበት ተጨማሪ የአሠራር ሥርዓት</u>

7.1 ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በቫወቸር ሥርዓት ለመጠቀም በአዋጅ ቁጥር 543/1999 የተጠቀሱትንና በዚህ መመሪያ የተገለፁ ሁኔታዎችን (መስፈርቶችን) ማሟላት አለባቸው፣

7.2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 7.1 ከተጠቀሰው በተጨማሪ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን ከቀጥተኛ ላኪው ጋር ያደረጉትን በሰነድ ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተረጋገጠ የዕቃ አቅርቦት ስምምነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይህም ውል ከሌሎች መካከል ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ያመረተውን ጥሬዕቃ ወይም የመጨረሻ ምርት ለቀጥተኛ ላኪው ካስረከበ በኋላ በዚህ ጥሬዕቃ የተመረተውን እና ቀጥተኛ ላኪው የተረከበውን የመጨረሻ ምርት ወደወጭ የመላኩ፣ ካልተላከም ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ቀጥተኛ ላኪው መሆኑን መግለፅ አለበት፡፡

7.3. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጥያቄውን ከገመገመ በኋላ ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬዕቃውን ለማምረት ከውጭ በሚያስመጣው ግብአት ላይ ሊከፈል በሚገባው ቀረጥና ታክስ ልክ ቫውቸር እንዲሰጠው፣ ለጉምሩክ ባለሥልጣን በደብዳቤ ሲገልፅ፣ በውሉ ስሙ ለተጠቀሰው ቀጥተኛ ላኪም በግልባጭ ያሳውቃል፣

7.4. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ለቀጥተኛ ላኪው በስምምነታቸው መሠረት ጥሬ ዕቃውን (ግብዓቱን) ሲያቀርብ በአንቀጽ 6(ለ)(4) በተመለከተው መሠረት በአገር ውስጥ የሚከፈሉ ታክሶችን መሰብሰብ አለበት::

7.5. ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው ጥሬዕቃዎቹን በቫውቸር ወደአገር ለማስገባት እንዲፈቀድለት ጥያቄ የሚያቀርበው የሚከተለውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ይሆናል::

ሀ. የማመልከቻው አቀራረብ እና የቫውቸር ፈቃድ አሰጣጡ በዚህ መመሪያ በተመለከተው የቫውቸር አሠራር ሂደት መሠረት ይከናወናል:: ሆኖም ከውጭ አገር ያስገባውን ጥሬዕቃ ባለበት ሁኔታ ለቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ላልሆኑ ላኪዎች የሚያቀርብ አስመጪ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችለው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በሚሰጠው ቫውቸር ዋጋ ልክ የኢንሹራንስ ቦንድ ሲያቀርብ ይሆናል፣

ለ. የቫውቸር አሰጣጥ ለቀጥተኛ ላኪ የተዘረጋውን የቫውቸር አሰጣጥ ሥርዓት በመከተል በጉምሩክ ባለሥልጣን ይከናወናል፣

ሐ. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርበውን ግብዓት የሚያመርት ከሆነ በሥርዓቱ ተጠቅሞ ለዚሁ ዓላማ

ያስገባቸውን ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም ያመረተውን ግብዓት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለቀጥተኛ ላኪ ማቅረብ አለበት:: በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ እንዲከፍል ይደረጋል::

መ. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ከውጭ የገዛቸውን ጥሬ ዕቃዎች ባለበት ሁኔታ በግብዓትነት ለቀጥተኛ ላኪው የሚያቀርብ ከሆነ በስምምነታቸው መሠረት ጥሬዕቃው ወደአገር በገባ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥሬ ዕቃዎቹን ለላኪው ማስረከብ ያለበት ሲሆን፣ ጥሬ ዕቃዎቹን ለቀጥተኛ ላኪው ማስረከቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ቫውቸሩ ተወራርዶ ለዋስትና ያስያዘው የኢንሹራንስ ቦንድ እንዲለቀቅለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል:: ቀጥተኛ ላኪውም በነዚህ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ ምርቶችን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም የጉምሩክ ባለሥልጣን ጊዜውን አራዝሞ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ ካልላከ ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ እንዲከፍል ይደረጋል::

ሠ. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ አምራች ከሆነ በቫውቸር ተጠቅሞ ወደአገር ባስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች ያመረተውን ግብአት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለቀጥተኛ ላኪው ማስረከብ አለበት:: ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርቱን ለላኪው ካላስረከበ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ይከፍላል::

7.6 ቀጥተኛ ላኪው በስሙ የኤክስፖርት ትዕዛዝ ኖሮት ነገር ግን የማምረቻ ድርጅት ሣይኖረው ሲቀርና ቀጥተኛ ያልሆነውን ላኪ (ማምረቻ ያለውን) ሰው/ድርጅት ድጋፍ በሚፈልግበት ጊዜ:-

ሀ/ ቀጥተኛ ላኪውንና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪውን (አምራቹን) የሚያስተሳስራቸው የወጪ ምርቱን እንዲያመርትለት የተስማሙበት ስምምነት መኖር አለበት፡፡

ለ/ ቀጥታ ላኪውና ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪው (ምርቱን የሚያመርትለት) ስምምነታቸውን በመያዝ ቫውቸር ደብተር እንዲሰጣቸው በጋራ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡፡

ሐ/ የቫውቸር ደብተር ጥያቄ ሥነ-ሥርዓቱን በመከተል መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ጥያቄ በሁለቱ መካከል ያለውን ስምምነት (ትስስር) የሚገልፅ መሆን አለበት፣ የቀረበው ማመልከቻም በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውሣኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

መ/ የቫውቸር ደብተር አሰጣጡም በቀረበው ስምምነት መሠረት ለሁለቱም በጋራ በጉምሩክ ባለሥልጣን ይከናወናል፡፡

ሠ/ ጥሬ ዕቃው ከውጪ ወደሀገር ውስጥ በመግባት ወደአምራቹ (ቀጥተኛ ያልሆነ) ላኪ በመተላለፍ ምርቱ ከተመረተ በኋላ ምርቱ ወደ ውጭ መላክ አለበት፡፡ በመላኪያው ቢል (Shipping Bill) ላይ የቀጥታ ላኪውና የቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ ስም መኖር አለበት፡፡

ረ/ ከሀገር ውስጥ ለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል፣ ለዚህም ስምምነታቸውንና ዕቃው ወደ ውጪ የተላከበትን ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡

ሰ/ በጋራ ለተረከቡት ቫውቸር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

7.7 በማናቸውም ምክንያት ከዚህ በላይ በአንቀጽ 7.6 በተዘረጋው ሥርዓት ለመጠቀም የማይፈልግ ቀጥተኛ ላኪ በአማራጭ ከዚህ በታች በተመለከተው ሥርዓት መጠቀም ይችላል፡፡

ሀ/ ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ቫውቸሩን በጋራ ለመጠየቅ ፈቃደኛ ካልሆነ በአንቀጽ 7.5 እንደተጠቀሰው ሁለቱን የሚያስተሳስር በሰነድ ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ስምምነት ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ ቀጥተኛ ላኪው ስምምነቱን በማያያዝ በራሱ ስም ቫውቸር እንዲፈቀድለት ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን መጠየቅ አለበት፡፡

ሐ/ የማመልከቻው አቀራረብ ለዚሁ ተግባር የተዘረጋውን አሠራር በመከተል ይፈፀማል፡፡ ቫውቸሩም ከጉምሩክ ባለሥልጣን የሚሰጠው ለቀጥታ ላኪው ብቻ ይሆናል፣ ቀጥታ ላኪውም ኤክስፖርቱን ለመፈፀም በግሉ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ፈቃዱ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲሰጠው ምርቱ ቀጥተኛ ላኪ ባልሆነው እንደሚመረት መገለፅ (መመልከት) አለበት፡፡

መ/ ምርቱን ለማምረት በሚያስፈልገው ከውጭ አገር በሚያስመጣው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በቫውቸር እንዲከፈል በማድረግ ምርቱን ወደውጭ መላክ አለበት፡፡

7.8. ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎች ከሀገር ውስጥ ለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች የተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት ይጠበቅላቸዋል፣ ለዚህም ስምምነታቸውንና ያመረቱትን ምርት ለቀጥተኛ ላኪ ያስረከቡበትን

ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡ ሆኖም ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት የታክስ ማቀናነስ ሥርዓት ተጠቃሚ ከሆነ የተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት አይኖረውም፡፡

7.9. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(ሠ)(1) እና (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ቫውቸሩን ለማወራረድ በአንቀጽ 6(ሠ)(3) የተዘረዘረውን መረጃ እንዲያቀርብ አይጠየቅም፡፡ በመሆኑም ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ በቫውቸር ወደአገር ባስገባው ጥሬ ዕቃ ያመረተውን ግብአት ለቀጥተኛ ላኪው ማስረከቡን የሚያስረዳ የሽያጭ ደረሰኝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማስረጃ ካቀረበ በቂ ይሆናል፡፡

## 8. <u>የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት</u>

### ሀ. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣

2. በላኪነት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣

3. ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጥሬ ዕቃ የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣

4. በመላክ ንግድ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ምርታቸውን የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣

5. ከውጭ ያስመጡትን ጥሬ ዕቃ ባለበት ሁኔታ ምርታቸውን ወደውጪ ለሚልኩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች የሚያቀርቡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣

6. ቀረጥ ከፍለው ያስገቡት ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ የተሳሳተ፣ የተበላሸ፣ የጐደለ ወይም ገዢ ያጣ በመሆኑ ምክንያት ወደመጣበት አገር መልሰው የሚልኩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች፣ እና

7. በአገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን የወጪ ምርት ለማምረት ተግባር የሚጠቀሙ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

## ለ. የሥርዓቱ ዝርዝር አፈጻጸም፣

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ከውጪ አገር ባስገቧቸው ወይም ከአገር ውስጥ በገዟቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ የምርት መያዣ (መጠቅለያ ዕቃዎች) እና በአገር ውስጥ በተመረቱ ምርቶች ላይ መክፈል የሚገባቸውን ቀረጦችና ታክሶች በሙሉ ይከፍላሉ።

2. ቀረጥና ታክስ በተከፈለባቸው ዕቃዎች የተመረተው ምርት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደውጭ መላኩ ሲረጋገጥ ወደ ውጭ ለተላከው ምርት ለዋሉ ጥሬ ዕቃዎችና መጠቅለያዎች የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ለባለመብቱ ተመላሽ ይደረጋል።

3. ላኪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረጥ ተመላሽ ለማግኘት ከውጭ አገር በገቡት ወይም ከአገር ውስጥ በተገዙት ጥሬ ዕቃዎች እና መጠቅለያዎች የተመረተው ምርት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(ሐ) የተመለከቱትን ማስረጃዎች ኮፒ አሟልቶ እንደአግባብነቱ ለጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

4. የቀረቡት ማስረጃዎች እንደአግባብነቱ በጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም በፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከተመረመሩና ተመላሽ መደረግ ያለበት የቀረጥ እና ታክስ ልክ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(መ) በተገለፀው መሠረት ከተሰላ እንዲሁም የጉምሩክ ወይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የማስረጃዎችን ኮፒ ከኦሪጅናሉ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጠና ተመላሽ ቀረጥ የተከፈለበት መሆኑን በኦሪጅናሉ ማስረጃዎች ላይ ምልክት ካደረገ በኋላ ተመላሽ ቀረጡን ለባለመብቱ ይመልሳል፡፡

5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በተደነገገው መሠረት ወደአገር በሚገቡ እና አገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች እና በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄ የሚቀርበው እና ገንዘቡም ተመላሽ የሚደረገው በፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ሲሆን፣ የሌሎች ቀረጥና ታክሶች ስሌት የሚከናወነውና ተመላሽም የሚደረገው በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

## ሐ. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች፣

የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚዎች በጥሬ ዕቃና ማሸጊያዎች (መጠቅለያዎች) ላይ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ለማግኘት ጥያቄአቸውን እንደአግባብነቱ ለጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ዋናውን እና ኮፒውን አሟልተው ማቅረብ አለባቸው።

1. ወደውጭ የተላከውን ምርት ለማምረት ሥራ ላይ የዋሉ ከውጭ የገቡ ወይም በአገር ውስጥ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎችና ሌሎች ግብዓቶች ዝርዝርና የተወሰነ መጠን ወጪ ምርት ለማምረት የተጠቀመባቸውን ግብዓቶች/ የግብዓት ምርት ጥመርታ/ ለምሳሌ:-

   አንድ የቆዳ ጫማ፣ አንድ የቆዳ ጃኬት፣ አንድ መቶ ጠርሙስ የወይን ጠጅ፣ ወዘተ/ለማምረት ከእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች (inputs) የሚያስፈልገውን መጠን የሚያረጋግጥ በአምራቹ የተዘጋጀና በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማረጋገጫ የተሰጠበት መግለጫ፣ (ይህ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የግብዓት-ምርት ጥመርታ (Standard input-Output coefficient) ሲዘጋጅ የሚቀር ይሆናል)

2. ከውጭ አገር ለመጡ ጥሬ ዕቃዎችና መያዣዎች/ መጠቅለያዎች የዕቃውን መጠን፣ ዋጋ፣ የገባበትን ጊዜና የተከፈለውን የታክስ መጠን የሚገልፁ፣

- የጉምሩክ ዲክለራሲዮን
- ደረሰኝ (Commercial Invoice)
- ቀረጥ የተከፈለበት የጉምሩክ ደረሰኝ፣ እና
- የዕቃ ዝርዝር (Packing list)

3. በአገር ውስጥ ለተመረቱ ጥሬ ዕቃዎችና መያዣዎች፣

   - የዕቃውን መጠን፣ ዋጋ፣ የተገዛበትን ጊዜና የተከፈለውን የታክስ መጠን የሚገልፅ ደረሰኝ፣

4. ከውጭ አገር በገባውና አገር ውስጥ በተመረተው ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች የተዘጋጀው ምርት ለውጭ ገበያ መላኩን የሚያረጋግጡ፣

   - የጉምሩክ ዲክለራሲዮን፣
   - ደረሰኝ (Commercial Invoice )፣
   - የማስጫኛ ሰነድ (Bill of lading/Airway bill)፣
   - ምርቱ ከተላከ ከ3 ወር በላይ ከሆነ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ገንዘብ የተከፈለበት የባንክ ደረሰኝ (Bank Credit Advice)፣

## መ. የተመላሽ ቀረጥ ስሌትና አወሳሰን፣

1. የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆን ሰው ወይም ድርጅት የተከፈለን ቀረጥ ለማስመለስ ጥያቄውንና በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8(ሐ) የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች አሟልቶ እንደአግባብነቱ ለጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

2. እንደአግባብነቱ የጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ጥያቄው ተሟልቶ መቅረቡን ካረጋገጠ በኋላ የሚመለሰውን የቀረጥ ልክ ያሰላል፡፡

3. እንደአግባብነቱ የጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን የደረሱትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ፡-

   i. የቀረጥ ተመላሽ የተጠየቀበትን ወጪ ምርት የተወሰነ መጠን (Unit) ለማምረት ከእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች የሚያስፈልገውን መጠን /ለጊዜው በቀረጥ ተመላሽ ጠያቂው ቀርቦ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማጋገጫ በተሰጠበት መግለጫ መሠረት/፣

   ii. የተወሰነ መጠን (Unit) ለማምረት ለሚያስፈልገው ለእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች ለአንድ መለኪያ የተከፈለውን ዋጋ (Unit Price) (ጥሬ ዕቃው በተገዛበት ደረሰኝ ወይም በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ወይም በባንኩ ፈቃድ ላይ የተመለከተውን የጥሬ ዕቃ ዋጋ ከውጪ በገባው ወይም በአገር ውስጥ በተገዛው ጥሬ ዕቃ መጠን በማካፈል ከላይ በተራ ቁጥር i በተመለተው መጠን በማባዛት፣

   iii. በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ፣ እንደዚሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ በተርን ኦቨር ታክስና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃና ሌሎች ግብዓቶች ላይ የተጣለውን የታሪፍ ወይም የታክስ መጣኔ (rate) (በሽያጭ ደረሰኝ ወይም በጉምሩክ ዲክላራሲን ላይ የተመለከተ)፣

iv. የተወሰነ መጠን (Unit) ወጪ ምርት ለማምረት ሥራ ላይ በዋሉት ጥሬ ዕቃዎችና ሌሎች ግብዓቶች የተከፈለውን ቀረጥና ታክስ መጠን ያሰላል፡፡ (ለእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃ ከላይ ከi እስከ iii የተመለከቱትን በማባዛትና ውጤቶቹን በመደመር)፣

v. በተራ ቁጥር «መ» የተገለፀውን አሀዝ ወደ ውጭ በተላከው ወጪ ምርት/ጉምሩክ ዲክላራሲዮን ላይ በተመለከተው/ መጠን በማባዛት ለባለመብቱ መመለስ የሚገባውን የተመላሽ ቀረጥ ልክ ያሰላል፣

vi. ከላይ በተዘረዘረው መሠረት የተመላሽ ቀረጡን መጠን ለማስላት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣኑ ችግሩን መርምሮ አማራጭ የአሰላል ስልት ሊጠቀም ይችላል፣

4. እንደአግባብነቱ የጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በተዘረዘረው የተናጠል የተመላሽ ቀረጥ ስሌት መሠረት ተረጋግጦ የቀረበውን ሂሳብ በአንቀጽ 8.ለ.4 በተመለከተው መሠረት ከመረመረ በኂላ ተመላሽ ቀረጡ ለባለመብቱ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

## 9. <u>የማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት</u>

### ሀ. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

1. ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፣

2. የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ፣ እና

3. ከጉምሩክ ባለሥልጣን የፈቃድ ወረቀት የተሰጣቸው የማመረቻ መጋዘኖች ያሏቸው አምራቾች የማመረቻ መጋዘኖች ሥርዓት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### ለ. የሥርዓቱ ዝርዝር አፈጻጸም

የሥርዓቱ ዝርዝር አፈጻጸም በአዋጁ እና በአዋጁ አንቀጽ 21/1 መሠረት የጉምሩክ ባለሥልጣን ስለማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት አፈጻጸም በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 10. በላኪነት ንግድ ሥራ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች

በአገር ውስጥ የተመረቱ ምርቶችን ገዝተው ወደውጭ በመላክ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በአዋጁ የተቋቋመው የተመላሽ ቀረጥ መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት፡-

ሀ/ ወደ ውጭ የላኩት ምርት በአገር ውስጥ የተመረተ ሲሆን፣

ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8.ሐ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ሲያቀርቡ ይሆናል፡፡

## 11. በምርት ሂደት ላይ ስለሚደርስ ብክነት

1. ወደውጭ አገር የሚላክ ምርትን በማምረት ሂደት ሊባክን የሚችለው ጥሬ ዕቃ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6.ሠ.1 እና 8.ሐ.1 በተመለከተው መሠረት አምራቹ ባዘጋጀው መግለጫ ውስጥ ያለመካተቱ ሲረጋገጥ፣ የተወሰነ መጠን (Unit) ወጪ ምርት ለማምረት በሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ መጠን ላይ እንደ ምርቱ ባህሪ ከ7(ሰባት) በመቶ የማይበልጥ የብክነት መጠን ጨምሮ ማስላት ይቻላል፡፡

2. ሆኖም እንደ ምርቱ ባህሪይ ከ7 በመቶ በላይ የብክነት መጠን መጨመር ሲያስፈልግ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጉዳዩን በጥንቃቄ መርምሮ በልዩ ሁኔታ እስከ 20 በመቶ የብክነት መጠን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3. ይህ የብክነት ግምት አገር አቀፍ የግብዓት ምርት ጥመርታ (Standard Input-output Coefficient) መረጃ በንግድና ኢንድስትሪ ሚኒስቴር ሲዘጋጅ የሚቀር ይሆናል፡፡

## 12. የጊዜ ገደብ

ወደውጭ አገር ገበያ የተላከን ምርት ለማምረት ሥራ ላይ በዋለው ጥሬ ዕቃና ማሸጊያ ላይ የቫውቸር ዋስትና የተሰጠበትን የቀረጥ ሂሣብ ለማወራረድ ወይም ተመላሽ ቀረጥ ለማግኘት፣

1. ጥሬ ዕቃው ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ወይም በአገር ውስጥ ከተገዛበት ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በጥሬ ዕቃው የተመረተው ምርት ለውጭ ገበያ መላክ አለበት፣ ሥራ ላይ ያልዋለው የጥሬ ዕቃ ወይም ማሸጊያ መጠን ተቆጥሮ ለሚቀጥለው አንድ ዓመት አገልግሎት ላይ እንዲውል የጉምሩክ ባለሥልጣን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2. ባለመብቱ ጥሬ ዕቃው ወደአገር ውስጥ ከገባበት ወይም በአገር ውስጥ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ገደብ ወይም የጊዜ ገደቡ በጉምሩክ ባለሥልጣን የተራዘመ ከሆነ የጊዜ ገደቡ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን እንደአግባብነቱ ለጉምሩክ ባሥልጣን ወይም ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የተከፈለው ቀረጥ እንዲመለስ ካልተጠየቀ ተመላሽ ቀረጥ የመጠየቅ መብት እንደቀረ ይቆጠራል፡፡

## 13. በሕጉ የተወሰነውን የጊዜ ገደብ ስለማራዘም

የጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 21/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12/1 የተመለከተውን የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት ጊዜ ያህል ለማራዘም የሚችለው፡-

1. ኢንዱስትሪው የሚገለገልበት ማሽን በመሰበሩ ወይም በሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ምክንያት ድርጅቱ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ ሥራ ማቆሙ ወይም፣

2. በምርቱ የአመራረት ባሕሪይ ምክንያት ምርቱን ለማምረት የሚፈጀው ጊዜ ከአንድ ዓመት በላይ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ወይም፣

3. ጥሬ ዕቃው በዓለም ገበያ ላይ እጥረት ያለበት በመሆኑ ወይም ከፍተኛ የግዢ ትዕዛዝ በመኖሩ ምክንያት የተያዘ ስቶክ ሲኖር ወይም፣

4. ምርቱን የሚገዛው የውጭ ድርጅት ውሉን ማፍረሱ ሲረጋገጥና ሌላ ገበያ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ ወይም፣

5. በፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ምርቱን ለማምረት ወይም ለውጭ ገበያ ለመላክ የማያስችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ይሆናል፡፡

## 14. በስህተት የተወራረደ ወይም ተመላሽ የተደረገ ሂሳብ

በአዋጁ በተደነገገው መሠረት የተወራረደው የቫውቸር ሂሳብ ስህተት ያለበት መሆኑ ወይም ሊመለስ ከሚገባው በላይ በስህተት ቀረጥና ታክስ

ተመላሽ የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ እንደአግባብነቱ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ወይም የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ስህተቱ በታወቀ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በሂሳብ ማወራረድ ወቅት የተሠራውን ስህተት ለማረም እና የቀረጥና ታክሱን ሂሣብ ከሚመለከተው ሰው ወይም ድርጅት ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## 15. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 15/94 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 16. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በቫውቸር ተጠቅመው ወደአገር ባስገቡት ጥሬዕቃ ያመረቱትን ምርት አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ለቀጥተኛ ላኪዎች መሸጣቸው ከተረጋገጠ ሂሳቡ በዚህ መመሪያ መሠረት ይወራረዳል፡፡ በመሆኑም ምርቱን ለመረከባቸው ማረጋገጫ የሰጡ ቀጥተኛ ላኪዎች በተረከቡት ግብአት ያመረቱት ምርት ወደውጭ ለመላኩ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

## 17 <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

**ይህ መመሪያ ከ ______ቀን 2000 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡**

***አዲስ አበባ ____________ ቀን 2000 ዓ.ም***

***ሱፍያን አህመድ***
***የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት***
***ሚኒስትር***

## አባሪ

## የጥሬዕቃ አቅርቦት ውል

ይህ ውል በ ____________________ ከዚህ በኋላ «ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ» እየተባለ በሚጠራው እና በ____________________ ከዚህ በኋላ «ቀጥተኛ ላኪ» እየተባለ በሚጠራው መካከል ዛሬ _____ቀን ______ ዓ.ም በ __________ ከተማ ተፈፀመ::

1. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 543/1999 በተደነገገው መሠረት በቫውቸር ተጠቅሞ ወደአገር ባስገባው ጥሬዕቃ:-

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | ነጠላ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |

በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በማምረት ለቀጥተኛ ላኪው ለማስረከብ ተስማምቷል::

2. ቀጥተኛ ላኪው ከዚህ በላይ በተ.ቁ.1 በተዘረዘሩት ግብአቶች ተጠቅሞ የሚያመርተውን ምርት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተስማምቷል::

3. ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ያመረታቸውን በተ.ቁ. 1 የተዘረዘሩ ግብአቶች ለቀጥተኛ ላኪው ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ለእነዚህ ግብአቶች ማምረቻ በቫውቸር ወደአገር ባስገባቸው ጥሬዕቃዎች ላይ ሊከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ ሙሉ ኃላፊነቱን ቀጥተኛ ላኪው ይወስዳል::

4. ቀጥተኛ ላኪው ቀጥተኛ ካልሆነው ላኪ የተረከባቸውን ግብአቶች ተጠቅሞ ያመረታቸውን ምርቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደውጭ አገር በመላክ ቫውቸሩን ለማወራረድ እንዲሁም በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀጥተኛ ካልሆነው ላኪ ግብአት ያመረተውን ምርት ወደውጭ አገር ካልላከ ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ በቫውቸር ተጠቅሞ ወደአገር ባስገባው ጥሬዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ለመክፈል ግዴታ ገብቷል፡፡

5. ሁለቱ ተዋዋዮች ቀጥተኛ ያልሆነው ላኪ ይህንን ውል ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በማቅረብ አምርቶ ለቀጥተኛ ላኪው ለሚያቀርባቸው ግብአቶች ማምረቻ ወደአገር በሚገቡ ጥሬዕቃዎች ላይ ለሚከፈለው ቀረጥና ታክስ ዋስትና የሚሆን ቫውቸር እንዲወስድ ተስማምተዋል፡፡

ይህ ውል በ ________ ኮፒ ተዘጋጅቶ ለተዋዋዮች፣ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ይሰጣል፡፡

| ____________________ | ____________________ |
|---|---|
| ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ | ቀጥተኛ ላኪ |

<u>ምስክሮች</u>

1. ________________
2. ________________